የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፪
አዲስ አበባ–መስከረም ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

5th Year No. 2
ADDIS ABABA - 9th October, 1998

## ማውጫ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፵፪/፲፱፻፺፩ ዓ.ም
የውሃ ሥራዎች ዲዛይን እና ቁጥጥር ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ........................ ገጽ ፰፻፶፫

## CONTENTS

Council of Ministers Regulations No. 42/1998
Water Works Design and Supervision Enterprise Establishment Council of Minister Regulations No. 1998 ........................ Page 853

### <u>የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፵፪/፲፱፻፺፩</u>
### <u>የውሃ ሥራዎች ዲዛይን እና ቁጥጥር ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት ልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ በአንቀጽ ፵፯/፩/(ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል ።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ ደንብ "የውሃ ሥራዎች ዲዛይን እና ቁጥጥር ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፵፪/፲፱፻፺፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· <u>መቋቋም</u>

፩· የውሀ ሥራዎች ዲዛይን እና ቁጥጥር ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅቱ" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል ።

፪· ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል ።

### *COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS No. 42/1998*
### *<u>COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE WATER WORKS DESIGN AND SUPERVISION ENTERPRISE</u>*

*These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 and Article 47 (1) (a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.*

1. *Short title*

   These Regulations may be cited as the "Water Works Design and Supervision Enterprise Establishment Council of Minister Regulations No. 42/1998"

2. *Establishment*

   1) The Water Works Design and Supervision Enterprise (hereinafter "the Enterprise") is hereby established as a public enterprise.
   2) The Enterprise shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

፫· ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን

የውሀ ሀብት ሚኒስቴር የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል ።

፬· ዋና መሥሪያ ቤት

የድርጅቱ ዋና መ/ቤት በአዲስ አበባ ይሆናል ። እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሊኖረው ይችላል።

፭· ዓላማ

ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው።

፩· የሀይድሮሊክስ ፣ የግድብ ፣ የመስኖ ፣ የመጠጥ ፣ የኢንዱስትሪ ፣ የፍሳሽ ማስወገጃ ውሀ ሥራዎችን እና የተፋሰስ ልማት ጥናቶችን ማካሄድ ፤

፪· የሀይድሮሊክስ ፣ የሀይድሮፓወር ፣ የጂዎቴክኒክ ፣ የግድብ እና የመስኖ ውቅሮች ፣ የጎርፍ ቁጥጥር ፣ የመጠጥ ውሃ ፣ የፍሳሽ ማስወገጃ እና የመሳሰሉትን የውሀ ሥራዎች የቅየሳ የዲዛይን እና የኮንስትራክሽን ሥራ ዝርዝሮችን ማከናወን ፤

፫· የውሀ ሥራዎች የውሉ አስተዳደር ቁጥጥርን በተመለከተ የአማካሪነት አገልግሎት መስጠት ፤

፬· የውሀ ሥራዎችን የሚመለከቱ ጥናቶች እና ዲዛይኖችን የመገምገም አገልግሎት መስጠት ፤

፭· የውሀ ሥራዎችን በሚመለከት የጨረታ ሠነድ እና ውል የማዘጋጀት ፤ ሥራ ተቋራጮችን የመምረጥ አገልግሎት መስጠት ፤

፮· ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎችን ማካሄድ ።

፮· ካፒታል

ለድርጅቱ የተፈቀደ ካፒታል ብር ፴፭ ሚሊዮን ፪፻፴፭ ሺህ ፮፻፸፪ ከ0፬ ሣንቲም (ሠላሣ አምስት ሚሊዮን ሁለት መቶ ሠላሣ አምስት ሺህ ስድስት መቶ ሰባ ሁለት ብር ከዜሮ አራት ሣንቲም) ሲሆን ይኸው በጥሬ ገንዘብ እና በዓይነት በሙሉ ተከፍሏል ።

፯· ኃላፊነት

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም።

፰· ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል ።

፱· ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ ከመስከረም ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፩ ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ መስከረም ፳፱ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ·ም·

መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

3. Supervising Authority

The ministry of water resources shall be the supervising authority of the Enterprise.

4. *Head Office*

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere as may be necessary.

5. *Purposes*

The purposes for which the Enterprise is established are:

1) to conduct studies pertaining to hydraulics, dams, irrigation, water supply, industry, sewerage disposal water works, and basin development master plans;
2) to carry out surveys, designs and specifications regarding hydrualics, hydro power, geotechnic, dam and irrigation structures, flood control, water supply, sewerage disposal and other related water works;
3) to render consultancy services regarding contract administration and supervision pertaining to water works;
4) to render service regarding water works studies and design evaluation;
5) to render services regarding the preparation of bid and contract documents, and selection of contractors concerning water works;
6) to engage in other related activities necessary for the attainment of its purposes.

6. *Capital*

The authorized capital of the Enterprise is Birr 35,235,672.04 (thirty five million two hundred thirty five thousand six hundred seventy two birr and four cents) which is fully paid up in cash and in kind.

7. *Liability*

The Enterprise shall not be liable beyond its total assets.

8. *Duration*

The Enterprise is established for an indefinite duration.

9. *Effective Date*

These Regulations shall come into force on the 9th day of October 1998.

Done at Addis Ababa, this 9th day of October, 1998.

MELES ZENAWI
PRIME MINISTER OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE